# Learning by Ear 2013

**«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–«መዘዙን መቀበል»**

EPISODE 4: **«የቆሸሸ ገንዘብ»**

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Daniel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**<u>INTRO/OUTRO:</u> NARRATOR**

**<u>SCENE 1: ዳንኤል TALKS TO በለጠ</u>**

- **ዳንኤል (M, 16)**
- **በለጠ (M, 16)**

**<u>SCENE2: AT MSOTO’S PLACE</u>**

- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ብሩክ (M, 8)**

**<u>SCENE 3: ምህረት AT PUBLIC TAP</u>**

- **GIRL 1 (F, 16)**
- **GIRL 2 (F, 16)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **ዳንኤል (M, 16)**

## INTRO

## 1. NARRATOR:

ጤና ይስጥልን! ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ የሚቀርብላችሁ የሬዲዮ ድራማ ነው። ዛሬ የድራማው ሁለተኛ ዙር 4ኛ ክፍል ላይ እንገኛለን። እስካሁን ብዙ ነገሮች ሆነዋል። የምህረት መንታ ወንድሞች ቅዱስ እና ብሩክ ከጎረቤት ሀገር ላቦሪያ ተመልሰዋል። አክስታቸው እንደምታሳድጋቸው ቃል ገብተው ነበር። ነገር ግን ቃላቸውን የጠበቁ አይመስልም።:

## 2. EPISODE 1, LINES 92 – 94:

*ቅዱስ: ክፉ ነህ ብሩክ። ልክ ላቦሪያ ማዕድን ማውጫ እንዳሉት ልጆች።*

*ብሩክ: ቅዱስ፤ ስለ ማዕድን ማውጫው ለማንም መንገር የለብንም። ይህንን ነው አክስት ለምለም እና አቶ ካሳሁን የነገሩን።*

## 3. NARRATOR:

ልጆቹ በላቦሪያ የገጠማቸውን ከአዕምሮ የማይጠፋ  መጥፎ ተሞክሮ ብቻም አይደለም የአቶ ሙላቱ ቤተሰብ መጋፈጥ የሚጠበቅበት። የልጆቹ አባት አቶ ሙላቱ በስርቆት ወንጀል ተጠርጥረው አሁንም ፖሊስ ጣቢያ ነው የሚገኙት። የ15 አመት ልጃቸው ምህረት እንዲሁ የራሷ ችግር አለባት፤ ከክፍል ጓደኛዋ ዳንኤል ጋ የግብረ ስጋ ግንኙነት ከፈፀመች በኋላ አርግዛለች። ሆኖም ዳንኤል በጭካኔ  ከህይወቱ አሽቀንጥሮ ጥሏታል። ይህም ምህረትን ክፉኛ አስጨንቋታል:

## 4. EPISODE 3, LINES 107 – 114:

*ምህረት: በፍቅርሽ አበድኩኝ ስትል አልነበር። ታድያ አሁን ምን ሆንክ?*

*ዳንኤል: ምንም የሆንኩት ነገር የለም። አንቺ ግን በርግጠኝነት የሆነ ነገር ሆነሻል። ላላደረጉት ነገር ደግሞ ምንም አይነት ኋላፊነት አልወስድም። (…) ምህረት ይህን ነገር ማስወጣት አለብሽ።*

## 5. NARRATOR:

በእርግጥ ዳንኤል ነገሩን አቅልሎ ይሆን የሚያየው? የዛሬው የጭውውት ክፍል "የቆሸሸ ገንዘብ" የሚል ርዕስ ይዟል። ዳንኤል ወደ ወንዶች ማደሪያ መግቢያው ላይ ሳለ የሚሆነውን እንከታተል። …

**<u>SCENE 1: ዳንኤል TALKS TO በለጠ</u>**

**6. ATMO: INSIDE BONGO HIGH DORMITORY, EVENING**

**7. SFX: KNOCK ON DOOR**

**8. ዳንኤል:** በሩን ክፈትልኝ በለጠ! ላናግርህ እፈልጋለሁ።

**9. SFX: DOOR OPEN**

***KW BEGIN***

**10. በለጠ:** **(not very friendly)** ሄይ ዳንኤል፤ ምን ሆነህ ነው?

**11. ዳንኤል:** አሁኑኑ ላናግርህ እፈልጋለሁ።

**12. በለጠ:** ስራ ላይ ነኝ።

**13. ዳንኤል:** ተው እንጂ  በሌ። ጎረቤት እና የአንድ ክፍል ልጆች ብቻ ሳንሆን ጓደኞሞች የሆንን መስሎኝ ነበር።!

**14. በለጠ:** እውነቱን ለመናገር አንተ ነህ ቀስ እያልክ ፊት የነሳኸኝ። ስለዚህ ከሌሎች ልጆች ጋ መሆን ፈልገህም ከሆነ ችግር የለብኝም።

**15. ዳንኤል:** እንደዛ አይደለም። ተሳስተሀል። እመነኝ ። አሁን ርዳታህ ያስፈልገኛል።

***KW END***

**16. በለጠ:** እሺ፤ ድምፅ ማሰማትህን ቀንስና ወደ ውስጥ ግባ፤ ዳኒ።

**17. SFX: FOOTSTEPS AS ዳንኤል ENTERS**

**18. SFX: DOOR CLOSES**

**19. በለጠ:** ተቀመጥ። ይቅርታ እንግዲህ ምንም የማቀርብልህ ነገር የለኝም። የኪስ ገንዘቤን ከጨረስኩ ትንሽ ሰነባበትኩ። ጓደኛዬ ዳንኤል ደግሞ ያለውን ሊያካፍል ፍቃደኛ አልነበረም።

**20. SFX: ዳንኤል SITS DOWN ON BED WITH SPRINGS**

**21. ዳንኤል:** በጣም አዝናለሁ በሌ። አንዳንድ የሚረብሹኝ ነገሮች ስለነበሩ ነው።

**22. በለጠ:** ምን?

**23. ዳንኤል:** ምህረት

**24. በለጠ:** በለው! አሁንም ስለእሷ!

**25. ዳንኤል:** በለጠ – አርግዛለች!

**26.** በለጠ: ምን? ከምርህ ነው? **(realizes)** እንዴ!ለዚህ ነው ሁልግዜ ሁለታችሁ እንደዛ መነታረክ  የጀመራችሁት። ወይኔ! ወንድሜን። እንዴት ያበሳጫል ባክህ።

**27.** ዳንኤል: ምን እንደማደርግ ግራ ገብቶኛል በለጠ። እሷ ደግሞ እኔን እየወቀሰች ነው።

**28.** በለጠ: እውነቱን ለመናገር ልክ ነች። አይመስልህም?

**29.** ዳንኤል: **(annoyed)** ግን አንተ ለመሆኑ ለማን ነው የምታግዘው?

**30.** በለጠ: ምንም አይነት መከላከያ አልተጠቀማችሁም?

**31.** ዳንኤል: ኮንዶም ማለትህ ነው? **(insecure)** አይ! ማለቴ… አንዴ ብቻ ስለሆነ ያደረግነው ምንም ይከሰታል ብዬ አልገመትኩም።…

**32.** በለጠ: እንዴት እንደዚህ ያለ አዕምሮው የሠላ  ሰው ደደብ ይሆናል! ያለመከላከያ ስታደርግ ስንት ነገር ሊከሰት ይችላል።! ስለ ኤድስ እንኳን አታስብም፣ ቂጢኝ አለ፣ ጨብጥ--

**33.** ዳንኤል: **(not amused)** እሺ እሺ የምትለው ገብቶኛል። ከእናቴ ጋ የማወራ መሰለኝ እኮ!

**34.** በለጠ: **(seriously alarmed)** ምን? እናትህ ከአንተ ጋ ስለእንደዚህ አይነት ነገር ያወራሉ?

**35.** ዳንኤል: **(laughs a little)** ትቀልዳለህ እንዴ? ስለ ግብረ ስጋ ግንኙነት እንኳን ከኔ ጋ አታወራም። - ምን እንደሆነ እንኳን የምታውቅ አይመስለኝም። ብቻ እንደ አዋቂ አታውራ ለማለት ፈልጌ ነው።

**SILENCE**

**36.** በለጠ: እና አሁን ምን ልታደርግ ነው?

**37.** ዳንኤል: አላውቅም። እኔማ አስወጪው ብያት ነበር። እሷ ግን የምትሰማ አትመስልም።

**38.** በለጠ: ምናልባት ውድ ሆኖባት ይሆናል…

**39.** ዳንኤል: **(sighs, desperate)** ስማ! እኔ አሁን አባት ልሆን አልችልም። እማዬ እንኳን አስረግዤ ከአንዷት ልጅ ጋ መተኛቴን ብታውቅ ትገለኛለች ።

**40.** በለጠ: **(trying to cheer him up)** ይገሉሃል? እኔ ደግሞ እናትህ የተባረኩ መስለውኝ ነበር።

**41.** ዳንኤል: **(laughs bitterly)**

**42.** በለጠ: ባክህ እሳቸው ሊያውቁ አይችሉም። እንደሚመስለኝ ! ለምህረት ፅንሱን የምታስወርድበት የተወሰነ ገንዘብ ብትሰጣት ይሻላል።

**43.** ዳንኤል: አዎ! አየህ እሱ ሌላው ችግር ነው። አገራችን ውስጥ ጦርነት ከተቀሰቀሰ ጀምሮ አባቴ በቂ ገንዘብ አይልክልኝም። ገበያ ቀንሷል ይላል፣ በዛ ላይ ገንዘብ ለመላክ አልቻለም። አብዛኞቹ ባንኮች ተዘግተዋል። ግን ዛሬ የተወሰነ ገንዘብ እንደሚልክልኝ ነግሮኛል።

**44.** በለጠ: በቃ! በኋላ ሆዷ መታየት ሳይጀምር ገንዘቡ እንደደረሰህ ስጣትና ታስወጣው።

***KW BEGIN***

**45.** ዳንኤል: **(sighs)** ጥሩ። እስቲ ርዕሰ መምህርቷ ጋ ሄጄ ገንዘቡ ደርሶ እንደውሆነ እጠይቃለሁ። ግን ምህረትን አንተ ብታነጋግራትስ? እኔን ልትሰማኝ አልቻለችም።

**46.** በለጠ: እ... ይኸውልህ! ይህንን ራስብ ብቻህን መወጣት ያለብህ ይመስለኛል። ይህ በአንተ እና በሷ መካከል ያለ ነገር ነው።

***KW END***

**47. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 2: AT MSOTO’S PLACE</u>**

**48. SFX: TANDIKA SLUM ATMO IN THE EVENING, INDOORS**

**49.** ቅዱስ: ብሩክ?

**50.** ብሩክ: እ ! ቅዱስ?

***KW BEGIN***

**51.** ቅዱስ: እማዬ የት እንደሄደች ታውቃለህ?

**52.** ብሩክ: ወደ ፖሊስ ጣቢያ መሄድ አለብኝ ብላ ነው የወጣችው። ደግሞ በጣም ተናዳ ነበር።

**53.** ቅዱስ: ምህረትስ?

**54.** ብሩክ: ውሃ ልትቀዳ ሄዳለች።

**55.** ቅዱስ: በጣም እርቦኛል

**56.** ብሩክ: እኔም

***KW END***

**57.** ቅዱስ: ዛሬ ብዙም አላሳልክም። ጉንፋንህ ተወሀ እንዴ?

**58.** ብሩክ: ነው መሰለኝ። ግን አሁንም እዚህ ደረቴ ላይ ያመኛል።

**59.** ቅዱስ: ካልተሻለህ እማዬ አልጋ ላይ ወጥተህ ብተተኛ ይሻላል።

**60.** ብሩክ: (dismissive) እኔ ሴታሴት አይደለሁም። አክስቴ ለምለም ወንዶች ትንሽ ጉንፋን ስለያዛቸው ብቻ ገብተው አይተኙም ስትል አልሰማህም።

**61.** ቅዱስ: አክስቴ ለምለም መጥፎ ናት፤ አልወዳትም።

**62.** ብሩክ: ስለአክስቴ ለምለምን እንዲህ ማለት የለብህም። ምንም ቢሆን አክስታችን መሆኗን መርሳት የለብህም።

**63.** ቅዱስ: ግን እሷናት እዛ መጥፎ ሰውዬ ጋ የወሰደችን። እሱ ደግሞ እዛ ጭለማ ጉድጓድ ውስጥ ሲያፈጋን እና ሲቀጠቅጠን ነበር።

**64.** ብሩክ: ታውቃለህ። ስለእዛ ሁልጊዜ እንዳሰብኩ ነው።...

**65.** ቅዱስ: እነስ ብትል።

**66.** ብሩክ: ... ግን ለማምለጥ ችለናል!

**67.** ቅዱስ: አዎ! (pause - thoughtful) ብሩክ ላቦሪያ ስለሆነው ነገር ለእማዬ ልነግራት ፈልጌያለሁ...

**68.** **ብሩክ:** መናገር የለብንም ቅዱስ አታስታውስም?

**69.** **ቅዱስ:** አዎ ግን --

**70.** **ብሩክ:** አይሆንም! ሰውየው ለአንድ ሰው ብንናገር እንደሚገለን ነግሮናል።

**71.** **ቅዱስ:** እሺ **(determined)** ታውቃለህ ትልቅ ስሆን ፖሊስ መሆን እፈልጋለሁ። በየቀኑ ስፖርት እሰራና ከዛ ትልቅ ጡንቻ ይኖረኛል። ልክ ታንዲካ ፊልም ማከራያው ቤት እንዳየነው ራምቦ። ከዛ ወደ ላቦሪያ እሄድና ያንን ተቀጣጣሪ እይዝና ጓደኞቻችን ኪኪ ፣ቾምቤን እና እዛ ጉድጓድ ውስጥ ያሉትን ልጆች በሙሉ ነፃ አወጣቸዋለሁ።

**72.** **ብሩክ:** እኔ ደግሞ ቻክ ኖሪስን ነው ደስ የሚለኝ። ትልቅ ሞተር ሳይክሌን እየነዳሁ እነዛን መጥፎ ሰዎች በሙሉ ባም ባም ባም! እያደረኩ እጨርሳቸው ነበር። **(both start to laugh)**

**73. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: ምህረት AT PUBLIC TAP</u>**

**74. SFX: SLUM ATMO IN THE EVENING, OUTSIDE**

**75. SFX: TAP RUNNING, PLASTIC CONTAINERS BEING FILLED**

**76.** **GIRL 1:** **(quarrelling)** እኔ ነኝ እዚህ ቀድሜ የደረስኩት የኔ ጀሪካን መጀመሪያ ነበር።

**77.** **GIRL 2:** አይደለም እኔ እቀድምሻለሁ። ምህረት የኔን እንስራ እዚህ ጋ አይተሽ የለ?

**78. ምህረት:** **(calm)** ምን እንደሚያወዛግባችሁእንኳን አልገባኝም።እኔ የቀዳሁትን ውሃ እቤት አድርሼ እስክመጣ ድረስ የሆነ ሰው ሌሎች ጀሪካኖቼን በሙሉ ከሰልፉ አውጥቷቸዋል።

**79. GIRL 2:** **(mocking her)** እና አሁን ልታለቅሺ ነው? እዛ ቀይራችሁት ወደነበረው  ያሽበረቀው  ቤት ለምን አትመለሺም! ለምን ወደ ታንዲካ እንደተመለሽ እንኳን አልገባኝም።

***KW BEGIN***

**80. GIRL 1:** **(laughs)** አዎ! ለሁለት ደቂቃ ሀብታም ፣ ታዋቂ ሆኑና ከዛ ተመልሰው ደኸዩ፤ ምስኪን።

**81. GIRL 2:** **(laughs)** ወንጀለኛ እና ጠጪ አባት ኖረቸው ድሮስ እንዴት ብለው ሁል ጊዜ ሀብታም ይሆናሉ ብለሽ ነው።

***KW END***

**82. ምህረት:** **(unperturbed)** ውሃሽን ውሰጂ እና ከዚህ ጥፊ።

**83. GIRL 1:** እሺ **(ironically)** "ሀብታሟ ልጅ". **(both girls laugh)**

**84. SFX: TAP RUNNING, PLASTIC CONTAINERS BEING FILLED**

**85. GIRL 1:** **(to the other girl)** በይ ነይ እንሂድ።

**86. SFX: FULL CONTAINERS BEING LIFTED**

**87. SFX: FOOTSTEPS OF TWO PEOPLE LEAVING**

**88. ምህረት:** **(to herself)** ሌላ የሚያስጨንቀኝ የሌለ ይመስል!.ደደቦች!

**89. SFX: TAP RUNNING, PLASTIC CONTAINERS BEING FILLED**

**90. SFX: FAST APPROACHING FOOTSTEPS**

**91. SFX: ENVELOPE THROWN ON WET GROUND**

**92.** ዳንኤል: ያውልሽ። 150 ዶላር (ገንዘቡ) ፖስታ ውስጥ አለልሽ!

**93.** ምህረት: ዳንኤል እዚህ ታንዲካ ምን ትሰራለህ? ለምንድን ነው ደግሞ ገንዘቡን የምትወረውርልኝ።

**94.** ዳንኤል: ያውልሽ ገንዘቡ። ፅንሱን አስወርጂና ሰላሜን ስጪኝ ምህረት። የምልሽ ይገባሻል? ደግመሽ አክፍሌ እንዳትመጪ፣ እንዳትፅፊልኝ፣ ክፍል ውስጥ ደግሞ ሁለተኛ እኔን ለማናገር እንዳትሞክሪ።

**95.** ምህረት: ገንዘብህን ልትወስድ ትችላለህ። አልፈልገውም።

**96.** ዳንኤል: ጥሩ! እንግዲያውስ እዛው ቆሻሻ ውስጥ ተይው። ግን ነገሮች ሲባባሱ እያላዘንሽ እኔ ጋ እንዳትመጪ።

***KW BEGIN***

**97.** ምህረት: ዳንኤል በርግጥ አንተ ነህ? ይህ እኔ የማውቀው ዳንኤል ሊሆን አይችልም!

**98.** ዳንኤል: እኔ አሁንም ያው ነኝ። አንቺ ነሽ እንጂ የተቀየርሽው እና እኔን መውቀስ የጀመርሽው። ለዛውም ይኼኔ ምንም ለማያገባኝ ነገር።ምናልባት ከንጉሴ ይሆናል ያረገሽው።

**99.** ምህረት: ንጉሴ?

**100.** ዳንኤል: በይ ባክሽ እያንዳንዱ ሰው ያንቺ ፍቅረኛ እንደሆነ ያውቃል።

**101.** ምህረት**:** ንጉሴ ነክቶኝ እንኳን አያውቅም። አሁን አሁን ግን በአንተ ቦታ እሱ ቢኖር ኖሮ ብዬ እመኛለሁ። ለምን እንደሆን ታውቃለህ? እሱ ከልቡ ይወደኛል። እንዳንተ እንደ ቆሻሻ አይቆጥረኝም።

**102.** ዳንኤል**:** በይ ጊዜዬን እያቃጠልሽው ነው። የሆነ ቦታ እንተያያለን።

***KW END***

**103. SFX: FOOTSTEPS GOING AWAY**

**104.** ምህረት**:** **(hysterical)** አዎ! አይቀርም። በቃ ሂድ ጥፋልኝ፤ አንተ ፈሪ ። ቦቅቧቃ! በጣም ነው ያስጠላኸኝ ዳንኤልካሳሁን ።

**105. <u>OUTRO - NARRATION:</u>**

እንግዲህ ዳንኤል ጥሎ ሄደ...እኛም ለዛሬ የበማድመጥ መማር ድራማን እዚህ ላይ እናበቃለን። ምህረት መሬት ላይ የወደቀውን ገንዘብ ታነሳ ይሆን? ለምህረት ታናሽ ወንድሞች ቅዱስ እና ብሩክ ታሪኩ እንዴት ይቀጥላል? ስለዚህ ለማወቅ እስከሚቀጥለው ጊዜ መጠበቅ ሳይኖርባችሁ አይቀርም። እስከዛው ግን ይህንን ጭውውት dw.de/lbe ን ጎብኝታችሁ በድጋሚ ልታደምጡ ትችላላችሁ። ወይንም በፌስ ቡክ ገፃችን ላይ እስካሁን ስለሰማችሁት ተወያዩ። የእውነተኛውን አለም ርዕሰ ዜና መስማት ከፈለጉ ደግሞ የዶይቸ ቬለ የአማርኛውን ዝግጅት ይክፈቱና ይከታተሉ። እስከዚያው። ጤና ይስጥልን።